ፓኖራማ ቁጥር 61

የትዝብት አድማስ

የካቲት 22 2001 ዓም

## <u>የሼል ነዳጅ ማዳያዎችና የሙኣመር ጋዛፊ ልጅ</u>

የሊቢያው መሪ የሙኣመር ጋዛፊ ልጅ ሰይፍ- እስላም ጋዛፊ በቅርቡ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት÷ በጠቅላላው በኢትዮጵያ የሚገኙትን የሼል ነዳጅ ማዲያ ጣቢያዎችን እንደገዛቸው ሁሉም የመገናኛ ብዙሃን ገልፀዉታል ፡፡ የሊቢያው መሪ ልጅ÷ ከዋናው ከተማ ከአዲስ አበባ አንስቶ እስከ ገጠር የሀገሪቱ ከተሞች ድረስ የተዘረጉትን የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎችን ÷ ያለአንዳች ተቀናቃኝና ተቆጣጣሪ ÷ በብቸኝነትና በባለቤትነት ገዝቷቸዋል ማለት ምን ማለት ነው ? በሀገራችን የኢኮኖሚ÷ የመጓጓዥ÷ የፀጥታ÷ የኢንተሊጀንስ ÷ በጠቅላላው በኢትዮጵያ ደህንነትና ኅልውና ላይ የሚያመጣው አንደምታ ምን ሊሆን ይችላል ? በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት ደግሞ በሕዝባችንና በሀገራችን ላይ በሚከሰተው አደጋና ብሎም አደጋውንም ለመከላከል በሚደረገው ጥድፊያና ርብርቦሽ ሂደት ምን ሚና ሊጫዎት ይችል ይሆናል ? በሀገሪቱ የመከላካያ ተቋማትና ተግባራት ላይስ ምን አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችል ይሆናል ? እነኝህንና ሌሎቹንም መሠረታዊና አሳሳቢ ጥያቄዎችን በአሁኑ ጊዜ ሊመልስ የሚችል ማዕከላዊ ኃይል አለመኖሩን ብንረዳም ÷ ጥያቄዎቹን በኃላፊነት ሊመልስ የሚችል የለም ብለን ግን ይህንን አደገኛ ሁኔታ ሕዝቡ አውቆ እንዲወያይበት ከማድረግ ቸል አንልም፡፡ ይህም ሚና ደግሞ÷ ለኢሕአፓ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ÷ የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት ለመከላከል ኃላፊነት አለብኝ የሚል ዜጋ ሁሉ የሚያሳስበውና የሚወያይበት አደገኛ ሁኔታ እንደሆነ እናምንበታል፡፡

ለገሰ ዜናዊና ጓደኞቹ ቀድሞ ከሙኣመር ጋዛፊ የተለገሰላቸውን ውለታ ለመክፈል ሲሉ ለባለ ውለታቸው ልጅ ፥ የሼል ነዳች ማደያ ጣቢያዎችን በመስጠት የኢትዮጵያን ነፃነትና ጎልውና አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ከህደት መፈፀማቸው ፥ እንደ ዕንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ ተደርጎ የሚቆጠር አዲስ ክስተት ነው አንልም ። ከወያኔ ሰዎች አጥፍቶ የመጥፋት ዓላማና ግብ ጋር የተየያዘ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።በከሃድያን ተግባር ምክንያት ሀገራችን በዘለዓለማዊ መልኩ ፥ጠላቶቿ የመሥዋዕት ጠቦት እያደረጓት እንድትጠፋ አንፈልግም ። እንዲያውም ይህ ከስተት እየቀጠለ በሄደ ቁጥር ፥ የትግላችን ቱማታ፥ የመሥዋዕት ቁርጠኝነታችን ትርታ እየጨመረልን ነው የሚሄደው ። ሀገራችን የባዕዳን መዘባበቻና መጫወቻ ሆና እንደማትቀር፥የሕዝባችን ዕምነት የጠላቶቿ ሆድ ቁርጠት፥ የወዳጆቿ ደግሞ ምኞት እንደ ሆነ በዕርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ዛሬ ኢትዮጵያ ሀገራችን፥ የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የሩቅ አይዞሽ ባይ ወዳጅ አላት ለማለት የሚቻል ባይሆንም፥ሕዝቦቿ ተባብረው ፥ ኃይላቸውን አጠናክረው፥ ዘረኞችን ለመቋቋም የሚያስችላቸውን ጥንካሬ በማያሻማ መልኩ በሚያረጋግጡበት ወቅት ፥ ወዳጆቿ የእበዙ ፥ ጠላቶቿ እየመነመኑ እንደሚሄዱ በታሪክ የተረጋገጠ ክስተት ነው ። ለዚህም ይመስላል የቀደመው ኢትትዮጵያዊ ትውልድ በየታሪክ አጋጣሚው ተመሳሳይ ጥቃት ሲደርስበት ፥ የሚከተለውን ስንኝ ሲያሰማ የቆየው።

የአምባገነን ኃይል ሲላሽቅ፥ የዘረኞች ሥርዓት ሲሸማቀቅ፥
የቅኝ ገዥዎች ሬሳ በራሳቸው ደም ሲዳፍቅ፥
በኢትዮጵያ አርበኞች አፅም ተቀጥቅጦ ሲደቅ፥
የባዕዳን ተንኮል ሲጋለጥ፥ የሀገር ሻጭ ቋንጣ ሲርመጠመጥ፥
የጠባቦች ጥብቆ ሲተረተር፥ የባንዶች ከንቱ ተስፋ ሲሟጠጥ፥
የአድር ባይ ወገብ ሲውገረገር ፥ መሃል ሰፋሪው ሲደናበር፥
የመሰሪዎች ደባ ሲፍረከረክ፥ በቆፈሩት ጉድጓድ ሲገቡበት
የሀፍረትን በርኖስ ሲያጣፉ ፥ የቁጭት እከክ ሲፈክቱ፥

የአይበገሬዎቹ ኃይል ሲጠናከር÷ የዕምነት ፅናቱን በተግባር ሲያስመሰክር÷
የድል ተስፋ ሲያብብ ÷ በአቸናፊዉ ኃይል ሲከበብ ÷ ነፃነቱ ሲያስከብር÷

የሕዝቡ ኃይል ተጠናክሮ ጠላቱን እያጠቃ÷ ነፃነቱንም ያስከብራል።

ሁሉም ጠላት አፍሮ ተሸንፎ ይወገዳል
ኢትዮጵያን ማን ደፍሮ በሰላም ይኖራል?
የኢትዮጵያን ሕዝብ ቅስም ማን ይሰብራል? አንድነቱንስ ማን ይገምሰዋል ?

ይህ የትላንቱ ሕዝባዊ÷ብሔራዊና የአርበኝነት አመፅ ጥሪና አቋም ዛሬም ህያው ነው። ይህም የአመፅ ጥሪ÷ዛሬ በወያኔ ሰፈር የአርዕድ-አንቀጥቅጥ ሽብር እንደ ሚፈጥር የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለማወላወል ያምንበታል። ምክንያቱም÷እንኳንስ ፉት ሲሉት ጭልጥ የሚለው የዘረኞች ኃይልና ጉልበት ቀርቶ÷ በዘመኑ ኃያል የነበረውንም የሙሶሊንን ወረራ ÷ ጭፍጨፋና ጥቃት በመቋቋም የኢጣሊያ ፋሽስትን የጭካኔ አገዛዝ ድምጥማጥ አጥፍቶ ነፃነቱን ያስከበረ ሕዝብ በመሆኑ ነው።

ነጻጅ ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ሕይወትና ኀልውና የቱን ያህል አስፈላጊና ጠቃሚ ለመሆኑ ሁሉም ዜጋ የሚገነዘበው ስለሆነ ያንንን ለማብራራት መሞከር ጊዜ ማባከን ይሆናል ። ሆኖም ታዲያ ÷ በዚያ ላይ ማተኮርን ባንሻም ÷ የኢትዮጵያን የነዳጅ ማደያ ጣቢዎችን ሁሉ በባዕዳን እጅና ቁጥጥር የመሆኑን ነገር ግን እንዲያው እንደ ቀላል የንግድ ስምምነትና የኤኮኖሚ ውል ፍርርም እንደሆነ አንቆጥረውም።አንድ የውጭ ሀገር ዜጋ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገትና የንግድ እንቅስቃሴ ከመቆጣጠር አኳያ ብቻ እንደሆነ ሊቆጠር የሚገባውም አይሆንም ። በዕርግጥ ያ ሀገር በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስር ወድቋል ካልተባለ በስተቀር። በተጨባጭ ማስረጃ የተደገፈ ዕውነታ ማየት ከተቻለ ግን ደግሞ ዛሬ÷ በዕርግጥ ሀገራችን የአንድ ልዕለ ኃያል ሀገር የእጅ አዙር ቅኝ ተገዥ

ለመሆኗ ለክርክር የሚቀርብ ርዕስ አይደለም ። ይህ ሀቅ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ደግሞ ፥የአንድ የዐረብ ሀገር ዜጋ ፥ያውም የሞላና የተትረፈረፈ የነዳጅ ሀብት ያለው ሀገር መሪ ልጅ፥ በአውሮጳ ሀገራት በብልግናና በሥነ-ስርዓት ማጉደል ሲከሰስ የከረመ ሰው ፤ የሀገራችንን የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎች በብቸኝነት ይዞ እንዲቆጣጥር ዕድል ሲያገኝ ፥ ኢትዮጵያውያን ዜጎች በአርምሞ ሊመለከቱት የሚገባቸው ሀገራዊ ጉዳይ አይሆንም። ነገር ግን ደግሞ ፥መለስና ግብረ አበሮቹ ትላንትና የሞኣመር ጋዛፊን ዕርዳታ ለማግኝ ሲሉ፥ "እኛ የየመን ዐረቦች ነን" ማለታቸውንም ሊረሳ የማይችል የታሪክ ጠባሳ መሆኑን እናውቃለን ። ይህ የኢትዮጵያን የነዳጅ ማዳያ ጣቢያዎችን መቆጣጠር ፥ የሊቢያ መሪዎች በሀገራችን ህልውና፥ አንድነት፥ የግዛት ልዕልና ፥ እንዲሁም ነፃነት ላይ ያላቸውን የቆየ ፖሊሲና አጀንዳ ተግባራዊ ከማድረግ ጋር የተያየዘና የተቀነባበረ ብቻ ሳይሆን ፥ ወደፊት ጊዜ ጠብቆ ከሚፈነዳው ቦምብ መሰናዶ ጋር ተያይዞ የሚታይ ሊሆን ይገባል። ኢትዮጵያን እንዳልነበረች ለማድረግ በሚደረገው የቆየ ሴራ የመጨረሻውን ምዕራፍ ለመክፈት የሚደረግ ጥረትና ሂደት እንደሆነ መገመት አያስቸግርም።ከሃዲያን የወያኔ መሪዎች የኢትየጵያን መጥፋት ከሚፈልጉ ወገኖች ጋር ይህን ያህል እጅና ጓንት ሆኖ መስራትና መተባበር፥ የታሪክ ምፀትና እንቆቅልሽ ነው ተብሎ የሚታለፍ አይሆንም። መለስና ግብረ-አበሮቹ የተነሱበትን ዓላማ ከፍፃሜ ለማድረስ ወደ መጨረሻው ምዕራፍ የሚቀርቡበት ነው ብለው ስለሚገምቱ ፥ የሀገሪቱን ስትራተጂያዊ የነዳጅ ጣቢያዎች ቁጥጥር ለባዕድ ማስረከባቸው የተስፋቸው ዳቦ መጉረሻ አድርገው ስለሚቆጥሩት ነው።ይህንን ቢያስቡና ተግባራዊ ለማድረግ ቢጥሩ የሚያስገርም አይሆንም። ምክንያቱም፥ እንኳንስ የመላዋን ኢትዮጵያን ጥቅም ቀርቶ፥ "ነፃ" አውጥተነዋል ያሉትንም የትግራይን ሕዝብ ህልውናም ሆነ ዘላቂ ጥቅምና ክብር የሚጠብቅ ፥ የሚያስከብርና የሚያድን ባለመሆኑ ነው። ለምን ቢባል ? በእኛ ዕምነት፥ የትግራይ ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም፥ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም ጋር ተለይቶ የማይታይ ባለመሆኑ ነው።

መላውን የሀገሪቱን የነዳጅ ማከማቻ÷ማደያና ማሰራጫ ጣቢያዎችን በብቸኝነት በባዕድ ቁጥጥር ስር እንዲሆን ማድረግ ÷ ቢያንስ የሚከተሉት ብሔራዊ አደጋዎች በሀገራችን ላይ ይከሰታሉ ብለን እንሰጋለን፡፡

- ባዕዳን በተዘዋዋሪም ይሁን በቀጥታ የሀገሪቱን የመከላካያ ሠራዊት የመቆጣጠርና በቅርብ የመከታተል ኃይልና ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል ፡፡ የሀገሪቱ ብሔራዊ ነፃነትና ደህንነት አደጋ በሚወድቅበት ጊዜ÷ ሠራዊቱ የመከላከል እርምጃ እንዳያደርግ ተጽዕኖ ይደረግበታል፡፡ የአየር ኃይል በረራም ሊደየን ይችላል፡፡
- ባዕዳኑ በሚያስፈልጋቸው ጊዜና ሁኔታ በነዳጅ ዕጥረት ምክንያት ÷ የሀገሪቱን የንግድ እንቅስቃሴን÷የመጓጓዣ አውታሮችን÷ የመገናኛ መስመሮችን ወዘተ.... አገልግሎት እንዳይሰጡ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ብቸኛ የመቆጣጠር ኃይል ያገኛሉ ፡፡ በመላው ሀገሪቱ ሁከትና ሽብር እንዲቀሰቀስ ምክንያቶች ይፈጠራሉ፡፡

- የገበያ ግርግር ለሌቦች እንደሚያመች ሁሉ ÷ በዚህ ብሔራዊ ቀውስ መካከል ወያኔዎቹ ትግራይን ለማስገንጠል ያላቸውን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ያመቻቸዋል፡፡ "የአክሱም ሐውልት÷ለአማራው" ለጉራጌውና ለኦሮሞው ምኑ ነው" ያሉት አሳፋሪና አስተዛዛቢ ቃል ዕውን ይሆንላቸዋል ፡፡ ነፃነት አውጀናል ብለው ሲያሳውቁ በሊቢያ መሪነት መላው የዐረብ ዓለም ወዲያውኑ አዋጃቸውን በጭብጨባ ይቀበልላቸዋል፡፡ "የአዲሲቱን የትግራይን ሪፑብሊክ" "ነፃነት" ለመከላከል ለአለፉት18 ዓመታት ሙሉ ትግራይ ውስጥ የተከማቸው መሳሪያ መቀሌ ካለው የአየር ኃይል አይሮፕላንና የታጠቀ የወያኔ ሠራዊት ሃያ አራት ሰዓት ተጠንቅቆ -ነቅቶ ይጠብቃል፡፡ አስፈላጊ ከሆነም÷ወደ ቀሪዋ የኢትዮጵያ ግዛት ዘልቆ በመግባት ስትራተጂያዊ የሆኑትን ወታደራዊ ቦታዎች ያጠቃል ፡፡ የወያኔ አዝማሪዎችም÷

“ጓና እየ  ጓና÷ ጓና እየ ጓና ÷ብጀካ ፍቅርና፡” (ከፍቅራችን በስተቀር ባዕዶች ነን ማለት ነው)  እያሉ ይጨፍራሉ፡፡

- አንቀጽ 39  ለትግራይ ከሰራ ለእኛስ  የማይሰራበት ምን  ምክንያት ይኖራል? የሚሉ ወገኖች የወያኔን  ፈለግ ይከተላሉ ፡፡  እነርሱም በበኩላቸው ÷  መለስ ያስጠናቸውን መዝሙር እየዘመሩ ይሄዳሉ፡፡ እንደዚህም እያሉ ይጨፍራሉ፡፡

  “ ድኻን ኹኒ ኢትዮጵያ  ኻብ ቅድም መፍራስኪ”

  ( ከመፈረስሽ በፊት ኢትዮጵያ ደህና ሁኚ ) ማለት ነው፡፡

ከዚያ በኋላ÷ቀሪዋ ኢትዮጵያ÷ የቴዎድሮስ ያለህ ! የዮሐንስ ያለህ ! የምኒልክ ያለህ! እያለች ብትጮኽ ማን እንደሚደርስላት ወደፊት የሚታይ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከወዲሁ  ሁሉም ዜጋ የባዕዳኑን ሴራ ተጠንቅቆ መከታተልና የወያኔንም ርኩስ ዕቅድ ማክሸፍ  አለበት!